Choke Seminar Series 18

# ነገረ ብራና ፩

**በሰማኸኝ ታደለ**

የካቲት 27/2018 ዓ.ም | 8:00 @T/Iyesus Wakjira Hall

# ብራና፡ ምንድን ነው?

- ብራና ለስነ ጽሑፍ ማሳረፊያ ወይም ለፊደላት መሳያ የተዘጋጀ ሰሌዳ ነው።
- የሚዘጋጀውም ከተለያየ የእንስሳት ቆዳ ነው።
- ስለዚህ በአወጣጡ ዘዴና በስም አጠራሩ ቢለያይም በግዕዙ ሰሌዳ፣ ክርታስ፣ ሌቅ እየተባለ ሙያው የሚነገርለት ብራና የወረቀት ፋብሪካዎች ከመፈልሰፋቸውና የጽሕፈት መሣሪያዎች ከመቋቋማቸው በፊት ከድንጋይና ከእንጨት ሰሌዳ አገልግሎት ቀጥሎ ማንኛውም ጸሐፊ ሐሳቡን በጽሑፍ ለማስፈር በብዛት ይጠቀምበት የነበረ ቁስ ነው።
- የብራና ስነ ጽሑፍ በኢትዮጵያ ታሪክ ዕድሜ ቢኖረውም በበለጠ ዕድገቱ ጎልቶና ተስፋፍቶ የታየው በሃይማኖትና በግዛት መስፋፋት፤ በስልጣኔና በስነ ጽሑፍ ታላቅ እርምጃ ታይቶ በነበረበት በአብርሃ ወአጽብሐ ዘመነ መንግሥት ነው(መሰረት ስብሐት ለአብ፥ 1981)።

# ስለ ብራና ጽሑፍ ሐብታችን ከፕሮሴር ጌታቸው ኀይሌ

- *....ምዕራባውያን አንድ የእጅ ጽሑፍ ሲያዩ ብዙ ሳያገላብጡ ከዐሥራ ስድስተኛው ምዕት ዓመት በፊት የተጻፈ ጥንታዊ መጽሐፍ መኾኑን አረጋግጠው ይንከባከቡታል፤ ለትዕይንት፣ ለምርምር ካልኾነ ለሌላ ጉዳይ አይጠቀሙበትም ። በእኛ ሀገር ግን እንዲህ አይደለም። ቱሪስቶች እየገዙ ከሀገር ሲያወጧቸው ሲቆጩን አይታይም። ነገር ግን ከግዥ ውጪ እንኳን ብዙ የጥንት መጻሕፍት አብረው ተዘርፈዋል። የሀገር ቅርስ ስለኾኑ መዘረፍ የለባቸውም ። **በተለይ የአንዲት ደኻ ሀገር ንብረት የሀብታም አገሮችን ሀብታሞች የባሰውን ሲያበለጽግ ማየት እጅጉን ያሳምማል።** እንደሰማሁት አንዱ መጽሐፍ አንድ ሚሊዮን አውጥቷል። ከኢትዮጵያ የወጣው ከመቶ ብር ባልበለጠ ዋጋ ተሸጦ ሊኾን ይችላል። ከተወሰዱት ውስጥ አንዳንዶች ኢትዮጵያ ውስጥ ሌላ ቅጅ እንኳን እንዳላቸው አይታወቅም። ግን አንዳንድ ጊዜ ካልተዘረፉት የተዘረፉት በየቤተ መጻሕፍቱ በሰላምና በጤና እየኖሩ በምንጭነት የበለጠ አገልግለዋል። ምዕራባውያን የእኛን ታሪክ የጻፉልን፣ አገስት ዲልማን የግዕዝን መዝገበ ቃላት ያዘጋጀልን ከኢትዮጵያ የወጡትን እጅ ጽሑፎች በመመርመር ነው። የገዳማቱን ትተን ከኢትዮጵያ ቤተ መጻሕፍት ወመዘክር እንኳ የአንዳች የእጅ ጽሑፍ ለማግኘት ከመሞከር በምዕራቡ ዐዓለም ካሉት ከማንኛውም ቤተ መጻሐፍት መጻጻፍ ይቀላል። እንዳይዘረፉ ምን ማድረግ ይቻልል? በእናት ሀገራቸው ኾነው በሰላምና በጤና እየኖሩ በምንጭነት የበለጠ እንዲያገለግሉ ምን ማድረግ ይቻላል? ማለቱ ይሻላል። ምክንያቱም መጻሕፍቱ የሚጠፉት በመዘረፍ ብቻ ሳይኾን ተባይ ሲበላቸውና የዘመን ብዛት ሲያኃሳቁላቸው የሚደርስላቸው በማጣት ጭምር ነው። በጥንቃቄ ቢጠበቁም ለጥናት በተፈለጉ ጊዜ በቀላሉ አይገኙም(ጌታቸው ኀይሌ፣ 2012)።*

# የበራና ጽሑፍ ታሪካዊ እድገት

- ኢትዮጵያ በእጅ ሥነ ጽሑፍ ከዳበሩት አገሮች አንዷ ስትሆን በአገር ውስጥና በውጪው ዓለም ባላት የብራ መጻሕፍት ክምችት በአፍሪካ ውስጥ ተወዳዳሪ እንደሌላት ይነገራል(ፈቃደ ሥላሴ፣ 2002)።
- እነዚህ ከአገራችን አልፈው በባእዳን አገሮች የተትረፈረፉት የብራና መጻሕፍት እንደቀድሞው ጊዜ የቁም ጽሕፈቱ ሥራ ሣይቋረጥ ከሥር ከሥሩ የሚጨመርባቸው ቢሆን ኖሮ የሥነ ጸሑፉም ሙያ ስለሚስፋፉ የመጻሕፍቱና ብራና ማዘጋጃዎቹ መሳሪያዎቹም ቁጥር እየበዛ ይሔድ ነበር።

- ብዛቱ እንዲጨምር ወቅቱ ባያስገድዳቸውም የአገራችን የቀድሞው ምሁራን ዘወትር የሚገለገሉበትን መሣሪያና የአሠራር ዘዴ በጽሑፍ ለማስቀመጥ እንደዋዛ ስለሚያዩት ምንም ዐይነት ዋጋ አይሰጡትም ነበር።
- ጸሐፊያኑ ሁሉ የመጣፊያውን መሣሪያ ማለትም ቀለሙንና ቀንዱን እራሳቸው ስለሚያዘጋጁትና ሥራውንም ትኩረት ስለማይሰጡት ለሚመጣው ትውልድ ማስታወሻ እናቆይ አላሉም።
- የችሎታቸውን ፍሬ በሚያበረክቱበት ወቅት ስለ አገራችን የስነ ጽሑፍ መሣሪያዎች ማስታወሻ ቢተውልን ኖሮ ዛሬ ባላሳሰበን ነበር(ፈቃደ ሥላሴ፣ 2002)።

- በብራና ላይ ጽሑፍን ማስፈር የተጀመረው ምን ጊዜ እንደነበር፥ ጀማሪውስ ማን እንደነበር ለይቶ ለማወቅ ባይቻልም፤ በበርካታ የአገር ውስጥና የውጭ ሀገር ሊቃውንት የተለያየ ጥናት እያደረጉበትና አስተያየት እየሰጡበት እስከአለንበት እንደደረሰ የሚታወስ ነው(ሥርግው ሀብለ ሥላሴ፣ 1969)።
- ሆኖም ዛሬ በዘመናችን እንደደረስንበት ሳይኾን ሥነ ጽሑፍ በድንጋይ፣ በእንጨት፣ በከብት ብራኳና፤ በሌሎችም በመሳሰሉት ሁሉ ተጀምሮ እስከ ብራናና ወረቀት ዘመን ደርሶ እንመለከታለን።
- እንደሚሰማንም ከሆነ ጽሑፍ በድንጋይና በመሳሰሉት ልዩ ልዩ መገልገያዎች መጀመሩን ከተመራማሪዎች የጥናት ውጤት እንመለከታለን፡-

●**አንደኛው፡-**(ዘፍ፤ 11፥7-20)።

●ከባቢሎን ግንብ መፍረስ በኋላ እያንዳንዱ ነገድ የብቻው የኾነ ቋንቋ ይዞ ወደ አገሩ ሲመለስ የግል ቋንቋውን ለማዳበርና ከሌላው አስበልጦ ለመገኘት ሃሳቡን የሚያሳርፍበት ዘዴ እየፈለገ ስነ ጽሑፍን በጡብ ፤ በድንጋይና በእንጨት እንዲሁም በሰው አርኣያና በአራዊት መልክ እየቀረጸና እየተገለገለባቸው ቆይቶ አርኣያውን ለትውልድ እንዳስተላለፈ ይተረካል(ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፤ 1979)።

❑ **ሁለተኛው፥** የነዚህ ትውልድ ተመሳሳይ የኾነው **ሐሞራቢ** (ዘጸ፡24፥12)።

- **አራተኛ፡** በዘመነ ነቢያት (ኤር፡ 36፥22) ይላል።
- **አምስተኛው፡-** (ሉቃ፡ 4፥17)ይላል።
- **ስድስተኛው፡** በዘመነ ሐዋርያት ጳውሎስ በሮሜ ሳለ ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልእክቱ ‘‘ከአክርጳ ዘንድ በጢሮአስ የተውኩትን በርኖሱንና መጻሕፍቱን ይልቁንም **በብራና የተጻፉትን አምጣልኝ’’** ብሎ ጽፏል(2ኛ ጢሞ፡ 4፥13)።

# ጥንታዊው የእጅ ስነ ጽሑፍ ዕድገት

- የኢትዮጵያ ሥልጣኔ በር ከፋች ሳባውያን በመኾናቸው የመጀመሪያው ስነ ጽሑፍ የተተለመው በነዚሁ ነገዶች መኾኑ ብዙዎቹ ይናገራሉ።
- ሌላው ታሪክ ጸሐፊ ጀምስ ብሩስ “የኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ ጽንሰቱም ኾነ ልደቱ ከሳባው ያለፈ ሲኾን መዋዕለ ዘመኑም እጅግ የራቀ ነው” በማለት አትቷል።
- የሳባውያን የድንጋይ ላይ ስነ ጽሑፍ ከክርስቶስ ልደት በፊት ፩ ሺህ ዓመት ቅድሚያ እንዳለው ተረጋግጧል(ኢአቤታ፥ 1975፤ 10)።
- ከክርስቶስ ልደትም በኋላ በአገራችን እስከ አራተኛው ክፍለ ዘመን አገልግሎት ሲያበረክት ቆይቷል።



- ይህ በዚህ እንዳለ በሦስተኛው ክ/ዘመን የግእዙ ፊደል ጎልቶ ወጣ።
- ሆኖም ከዛ በፊት አልነበረም ለማለት ሳይኾን በሕዝብ ዘንድ ታወቀ ወይም አገልግሎቱን በስፋት አበረከተ ለማለት ነው።
- የግእዙ ጽሑፍ ከሳባው ለየት ብሎ እራሱን በመቻል የታየው ከሁለተኛው ምዕት አጋማሽ ጀምሮ መኾኑን በድንጋይ ላይ ከሰፈሩት ጽሑፎች ለማወቅ ተችሏል።



- የግዕዙ ስነ ጽሑፍ ፊደል አገልግሎቱን በመጀመሪያዎቹ ፊደላት ያለ አናጋሪ ያበረከት እንደነበረ በሸክላና በድንጋይ ላይ በሰፈሩት ጽሑፎች ተረጋግጧል።
- ፊደሎችም ግዕዞች ብቻ ነበሩ (EMMLNo. 8529) በነዚህ የመጀመሪያዎቹ የግዕዝ ፊደሎች በሦስተኛው ክ/ዘመን የተጻፈው ጽሑፍ በመጠራ ከሚገኘው ሐውልት የተቀረጸው ነው (በባሕል ሚኒስቴር 10ኛ መጽሔት)።
- አጻጻፉ ከግራ ወደ ቀኝ ሲኾን አንዱን ቃል ከሌላው የሚለይ አቆልቋይ መስመር /ዝባር/ አለው።
- ያ አቆልቋይ መስመር በኋላ ወደ **ሁለት** ነጥብ ተለውጧል።



- ጽሑፉ በይዘቱም ኾነ በአፍዓዊ መልኩ ከሳባው ተለይቷል የመጠራው የድንጋይ ላይ ጽሑፍ ግእዝ እያደገና እየተሻሻለ መሄዱን የሳያል።
- በዚሁ በሦስተኛው ምዕት ዓመት በተጨማሪ ሃይማኖታዊና ታሪካዊ ይዘት ያላቸው የግእዝ ጽሑፎች በብዛት ተገኝተዋል።
- በአራተኛው ክ/ዘመን በኢዛና ዘመነ መንግሥት እንደፊተኞቹ ዓይነት ማለትም በግዕዞቹ ፊደሎች ብቻ የተጻፈውን ሥነ ጽሑፍ “አዘነ ነገሠ አከሠመ” በሚል እናገኛለን።



- ትርጉሙም በአጭሩ ኢዛና ንጉሠ አክሱም ማለት ነው።
- አራተኛው ምዕት ለግዕዝ ፊደላት አጻጻፍ መሠረት የተጣለበት ዘመን ነው።
- ከፊተኞቹ ይልቅ ብዛት ያላቸው የድንጋይ ላይ ጽሑፎች የተገኙበት ብቻ ሳይኾን አናጋሪ ምልክቶች የጠፈጠሩበት ነው።
- ከዚያ በፊት የነበሩት ጽሑፎች የተጻፉት በደረቁ ግእዝ ብቻ ሲሆን አንባቢዎቹ **አናጋሪ ምልክቶችን** በልቡናቸው እየጨመሩ እንዲያነቡ ይደረግ ነበር(ፈቃደ ሥላሴ ተፈራ፣ 2002)።

በትግራይ ክ/ሀገር አባገሪማ ገዳም የሚገኘው አርባዕቱ ወንጌል እስከ ቅርብ ዓመታት ከታወቁት የብራና ጽሑፎች ጥንታዊው እንደኾነ ይታመናል።

ኾኖም በ1989 ዓ.ም በገዳሙ ዕቃ ቤት ላይ በደረሰው የእሳት አደጋ እንደተጎዳ ይነገራል።



AG 1: wooden boards (?), gilded copper covers. 353 x 264mm, 184ff. (AGI).



AG 2: wooden boards, leather, silver covers. 332 x 254 mm, 259 ff. (AGII), 162 ff. (AGIII).

- በ15ኛው መቶ ክ/ዘመን ከነበሩት የኢትዮጵያ መሪዎች ስመ ጥር የነበረው ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ (1426-1460) ሲኾን በዘመኑ የተአምረ ማርያምን መቅድም ደርሶ በቀዳማዊ ዳዊት ዘመን ከተተረጎመው ዐፄ ዳዊት ከአጻፈው ተአምረ ማርያም ጋር እንዲጠረዝ አድርጓል(EMML, 9002)።

- ይህ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የቀደምት አባቶቹን ፈለግ በመከተል ቅዱሳት መጻሕፍትን እያስተረጎመ አስጽፏል።

- ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ በማንኛውም ቤተ ክርስቲያን እሑድ እሑድና በሌሎች በዓላት ከቅዳሴ ውጪ ተአምረ ማርያም እንዲነበብ ሥርዐት አውጥቷል።



Ethiopian manuscript containing Miracles of Mary, 14th c. (EMML 9002)

- በ16ኛው ክ/ዘመን ዐፄ ልብነ ድንግል (1500-1533) ተአምረ ማርያም እያስጻፈ ለየአድባራቱ ያድል እንደነበረ ተረጋግጧል።

- ከአስጻፋቸውም መጻሐፍት ውስጥ በሰላሌ አውራጃ ቄሲ ኪዳነ ምሕረት ከምትባለው ደብር በራስ ዳርጌ አማካኝነት በስጦታ የተበረከተችው ተአምረ ማርያም ትገኝበታለች።

- በ16ኛው ክ/ዘመን መጀመሪያ ላይ የቀድሞዎቹ ብዙ መጻሕፍት ቢወድሙም የጠፉትን ለመተካት የቁም ጽሕፈት ውድድር የተጀመረበት ነው ሊባል ይችላል።

- የዐምዶችን መስተካከል፤ የመስመሮችን ስፋት መጠበቅ የተጀመረበትና የፊደሎችን የቅርጽ ውበት ለማየት የተቻለበት ዘመን ነው።

- የዳዊት መዝሙር በግዕዝ ቋንቋ በዘመናዊ መሣሪያ የተባዛው በዚሁ በአሥራ ስድስተኛው ክ/ዘመን መጀመሪያ ላይ ነው።

- ዐፄ ሠርፀ ድንግል (1563-1597) ዓ.ም ከደብረ ሊባኖስና ከዐፄ ልብነ ድንግል ቤተ መንግሥት የጠፉትን ንዋየ ቅድሳትና የብራና መጻሕፍት አስፈልጎ ከነ ሊቃውንቱ ከግንደ በረት ወደ ጎንደር ክ/ሀገር በማስወሰድ ጉንዶ መስቀልና ሺሜ ማርያም የተባሉትን አብያተ ክርስቲያናት መትከሉ ይታወሳል(ንጋቱ ውቤ፣ 1981)።
- በነዚያም አብያተ ክርስቲያናት የሚኖሩትን ሊቃውንት በየቀድሞ ሥራቸው በአሰማራበት ወቅት ብዙ ቁም ጸሐፊዎችን አሰልፎ ታላላቅ መጻሕፍትን ለጣና ገዳማትና ለጎንደር ክ/ሀገር ታላላቅ አድባራት ስላበረከተ መጻሕፈቱን በየገዳማቱ ለማግኘት ተችሏል(EMML, 1508).

- በክፍለ ዘመኑ መጨረሻ በጎንደር ዘመነ መንግሥት የግዕዝ ፊደላት ተለዋውጠውበታል፤ ሣልስ ቅጽል ወደ ሳድስ እየተለዋወጠ መጻፍ መጀመሩን በጊዜው የተጻፉት መጻሕፍት ይዘት ያስረዳል።
- በ17ኛው ክ/ዘመን የነበረው ታላቁ የጎንደር ንጉሥ ፋሲል ትኩረቱ በሕንፃ ሥራ ላይ ቢኾንም አልፎ አልፎ ያስጻፋቸው መጻሕፍት አልታጡም።
- በዚያው ክ/ዘመን መጨረሻ የነበረው አንደኛ ኢያሱ አድያም ሰገድ (1682-1706) ታላላቅ መጻሕፍትን አስጽፏል።
- ከመጻሕፍቱም ውስጥ በጎርጎራ አውራጃ በደብረ ሲና ማርያም የተመዘገበው ከመስከረም እስከ መጋቢት ያለውን ታሪክ የያዘ ስንክሳር ይገኝበታል።

- ዐፄ ኢያሱ የሚታወስበት ሌላው በደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተ መቅደስ ላይ ሥዕለ ማርያምን ሲያስል በሠዓሊዎቹ ፊት እጅግ በጣም እያለቀሰ "እኔ ኀጢአተኛውን እመቤቴ ከጌታየ እንድታማልጅኝና እንድታስምሪኝ ዕንባየን ከቀለሙ ውስጥ እየጨመራችሁ ሣሉልኝ" በማለት በእንባው አስሏል እየተባለ ይነገራል።
- ብዙ ቁም ጸሐፊዎችንም ከቤተ መንግሥቱ ግቢ አኑሮ የብራና መጻሕፍትን ያጽፍ እንደ ነበር ይነገራል።

- በአሥራ ዘጠነኛው ክ/ዘመን ከነገሡት ነገሥታት የብራና መጻሕፍትን በማስጻፍ ከፍተኛውን ደረጃ የያዙት ዳግማዊ ዐፄ ምኒሊክ ናቸው።
- በዐፄ ምኒሊክ ዘመነ መንግሥት ቁም ጸሐፊዎች ተቀጥረውና የቤተ መንግሥቱ ግብረ በላ ኾነው በመሥራታቸው የቁም ጽሕፈት ሥራ እንደገና የተስፋፋ መኾኑን በዘመናቸው የተጻፉት መዛግብት መስክረዋል።
- በተለይ የብራና መጻሕፍትን በእጅ እያስጻፉ ለአብያተ ክርስቲያናት ከማበርከታቸው ባሻገር ለታላላቅ የሠራዊት አለቆቻቸው ይሸልሙ እንደነበር ተረጋግጧል።
- ለምሳሌም ያህል ለንጉሥ ሚካኤል፣ ለራስ ወሌ፣ ለዋግሹም ከበደና ለልጅ ወንድ ወሰን ምኒልክ ሰጥተዋቸዋል።

- ዳግማዊ ምኒልክ በመላ ኢትዮጵያ በየክፍላተ ሀገሩ ለነበሩት ቁም ጸሐፊዎች ከመንግሥት የአሥራትና የቀረጥ ገቢ ከዐሥር አንድ እየተቀነሰ እንዲሰጣቸው ስላዘዙና እንደ አካባቢው አመቺነት ጋሻ መሬት ስለ ሰጧቸው የቁም ጽሕፈት ባለሞያዎች ከሌላው ሰው የተለየ ክብር ነበራቸው።
- ይህንንም ለማድረግ የወሰኑት ቁም ጸሐፊ በሕዝቡ ዘንድ የተናቀ በመኾኑ ሞያውን ለማስከበር ይመስላል።

- ኾኖም በአገር ውስጥ የሚደረገው በአንዳንድ የመሳፍንት ጦርነት ጊዜ መጻሕፍቱ ከአንድ ቤተ መቅደስ እየተዘረፉ ወደ ሌላው ቤተ መቅደስ ስለ ሚሄዱ መጻሕፍቱ ከመጥፋታቸውም በላይ በየመጻሕፍቱ ላይ የሰፈሩት አብዛኛዎቹ የማስታወሻ ጽሑፎች ይፋቃሉ።
- ከላይ የተገለጸውን ችግር ለመሸሸ አንዳንድ የደብር አለቆችና የገዳም አበምኔቶች የነገሥታት ወይም የልዩ ልዩ ገዥዎች ስም ወይም ማስታወሻ ያለበትን መጽሐፍ ሠውረው ተርታውን ነገር ያስጎበኛሉ።

- በአገር ውስጥ በተደረገው የእርስ በርእስ ጦርነትና የባዕዳን ጦርነት በተለያየ ኮረብታማ ቦታዎች ተቀብረው በተለያዩ ጊዜያት ቤተ ክርስቲያን ለማነጽ በተደረገው ቁፋሮ ከአፈር የተረፉ ንዋያተ ቅድሳት ተገኝተዋል።
- እነዚህ ሁሉ ሲታዩ በአንፃሩ ስንት የብራና መጻሕፍት እንደተቃጠሉ ወይም በከርሰ ምድር ተቀብረው እንደቀሩ ያመላክታሉ።
- በ16ኛው ክ/ዘመን በተደረገው የግራኝ መሐመድ ወረራ የኢትዮጵያ የብራና መጻሕፍት ከመቶ ሰማንያዎቹ ተቃጥለዋል ወይም ወድመዋል ብንል ከእውነት አንርቅም (ፈቃደ ሥላሴ፣ 2002)።

- በ19ኛው ክ/ዘመን በዐፄ ቴዎድሮስ ሞት ጊዜም ቁጥራቸው ከፍ ያሉ የብራና መጻሕፍት በእንግሊዞች ከመወሰዳቸውም በላይ በአሁኑም ጊዜ በእንግሊዝ አገር ሙዚየሞች እንዳሉ የታመነ ነው።
- በኋላም የባሕር በር ሲከፈት ፈረንሳዮች ከኢትዮጵያ ጋር ባደረጉት ወዳጅነት መሠረት በአገር ጎብኚዎችና በባለሥልጣኖች የሥጦታ ልውውጦች አማካኝነት መጽሐፎቻችን ወደ ፈረንሳይ ስለኮበለሉ ዛሬም የፈረንሳይን ሙዚየሞች በማዳበር ላይ ናቸው።

- ቀደም ሲል ወደ አገራችን የገቡት የኢጣልያ ወዳጆች የካቶሊክ እምነት ተከታዮች መምህራን የኢትዮጵያን የብራና መጻሕፍት ወደ ሮም ለመውሰድ በተለያዩ ክ/ዘመናት ያላደረጉት ጥረት የለም፤ ነገር ግን እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር 1928-1933 ዓ.ም በነበረው የኢጣሊያ ወረራ የኢትዮጵያን መጻሐፍት ለመዝረፍና የባቲካንን ሙዚየሞች ለማሟላት ዕድል አግኝተዋል።
- ታዲያ በአንድ በኩል ብራና አውጥቶ መጽሐፍን መጻፍ ወይም የመገልበጥ ሥራ በመነመነበት ጊዜ ምንጩ የደረቀውን የብራና መፍሐፍ ሲሸጥ መመልከቱ በአገር ውስጥ ይኖራል ተብሎ የተገመተውን የብራና መጽሐፍ ቁጥር ስለሚቀንሰው ሁኔታው አሳሳቢ ኾኖ ይታያል።

# በኢትዮጵያና በኤርትራ ያሉ የብራና መጻሕፍት ስብስቦች

Däbrä Bizän
570 mss.

Gunda Gunde
220 mss

Aksum Séyon
several hundreds

Tana Qirqos
> 200 mss.

Däbrä Häyq Ǝstifanos
200 mss.



# Overview of Gəʿəz manuscripts from Ethiopia and Eritrea




Source: [http://www.menestrel.fr/?-Inventaire-des-bibliotheques-et-des-catalogues-des-manuscrits-ethiopiens-&lang=en.](http://www.menestrel.fr/?-Inventaire-des-bibliotheques-et-des-catalogues-des-manuscrits-ethiopiens-&lang=en.)

| | |
|---|---|
| Austria | 52 |
| Belgium | 40 |
| Canada | 13 |
| Danemark | 5 |
| Egypt | 25 |
| Finland | 6 |
| France | 1049 |
| Ireland | 68 |
| Israel | 900 |
| Italy | 1480 |
| Norway | 50 |
| Poland | 21 |
| Russia | 173 |
| Swiss | 25 |
| Suede | 89 |
| Germany | 991 |
| Netherlands | 220 |
| UK | 946 |
| Peru | 19 |
| Turkey | 19 |
| Spain | 2 |

# Bibliotheca Apostolica Vaticana (Vatican City)

- possession: c. 1,100 mss
- collections
  - Vatican (= ‘Vat.et’, 336 mss)
  - Borgia (= ‘Borg. et.’, 37 mss)
  - Cerulli (= ‘Cerulli et.’, 330 mss)
  - Comboni (= ‘Comb’ 290 mss)
  - Raineri (= ‘Raineri’, 112 mss)
  - Rossi (= ‘Ross. 865’, 1 ms.)
  - Barberini (= ‘Barb or. 2’, 1 ms.)



Santo Stefano dei Mori, Vatican City



Enrico Cerulli (1898 - 1988)

- catalogues
  - Grébaut and Tisserant 1935, 1936
  - van Lantschoot 1962
  - Raineri 1998, 2000, 2004
  - Bausi 2012

# BIBLIOTECA APOSTOLICA VATICANA (VATICAN CITY)




- digitised mss: https://digi.vatlib.it/mss/ (browse by collection 'Vat.et', 'Cerulli et.',...)

# Bibliothèque nationale de France (Paris)

- **possession: c. 1,034 mss**
- collections
  - Éthiopien d'Abbadie (= 'Abb.'): 234 mss (1837– 1849)
  - Éthiopien (= 'Eth'.): c.750 mss
    - ❖ MSS acquired by the library since its foundation, new acquisitions
    - ❖ Mondon-Vidailhet collection (113 mss, collected between 1892–1897)
    - ❖ Griaule collection (366 mss, Dakar-Djibouti expedition in 1931–1933)
    - ❖ Cohen collection (44 mss)
    - ❖ Duchesne-Fournier collection (8 mss)



**Antoine d'Abbadie (1810 – 1897)**



**Casimir Mondon-Vidailhe (1847 – 1910)**



**Marcel Griaule (1898 -1956)**



**Marcel Cohen (1884 -1974)**

# Bibliothèque nationale de France




- digitised mss: [https://archivesetmanuscrits.bnf.fr/](https://archivesetmanuscrits.bnf.fr/)
  (ongoing digitisation, search for 'Éthiopien', the exact shelfmark,

# BRITISH LIBRARY (LONDON)

- Possession: c. 600 mss
- collections
  - collection by Karl Wilhelm Isenberg and Johann Ludwig Krapf: 82 mss, collected in the early 1840s 'Maqdalā' collection (looted in 1868 by the British army): **349 mss from Madane 'Ālam purchased by Richard Holmes** (= mss. Orient. 480–829); many other mss were carried away by soldiers and other members
  - manuscripts acquired after 1877, many of them also originating from Maqdalā, and 12 from the private collection of Robert Curzon



Karl Wilhelm Isenberg (1806–1864)



**Johann Ludwig Krapf (1810–1881)**



**Robert Curzon (1810 – 1873)**



**The End of King Tewodros II (*The Illustrated London News*, 1868)**

# British Library (London)

- digitised mss: https://www.bl.uk/collection-guides/ethiopian-collections (ongoing digitisation, searching for the keyword "ethiopic" yields many results, but not all - search for the shelfmark if looking for a particular manuscript)



# Digitised Manuscripts



- Important collections of digitised manuscripts:
  - EMML
  - (Ethiopian Manuscript Microfilm Library)
    - The c. 9600 manuscripts microfilmed by the EMML project in the 1970s-1990s in Ethiopia are partly made available through vHMML (virtual Hill Museum & Manuscript Library), and many of them can be accessed freely after creating an account

(https://www.vhmml.org/%3B https://hmml.org/about/global-operations/ethiopia/)

# በቁም ጽሕፈት የሚጻፉ መጻሕፍት

Based on the typologies (general format), manuscripts can be divided :

1. **The scroll (*volumen, kətab*)**
2. **The leporello-book (*sənsul*)**
3. **il codice (*codex, mäṣḥaf*)**







# የጥቁር ቀለም አወጣጥ፡-

ሀ. ጥላሸትና ከሰል፡-

- በመጀመሪያ ከልዩ ልየው ዕቃዎች ጥላሸትና ከሰል ይሰበሰባል፤ የምጣድ የድስትና የሌላም የማነቸውንም ይህን የመሳሰሉ ከእሳት የሚደርሱትን ዕቃዎች ጥላት ነው።
- የክትክታን ቅጠል አቃጥሎ ደቁሶ ከጥላሸቱ ጋር መቀላቀል፤
- የቀረጥን ቅጠል አቃጥሎ ከሰሉን ደቁሶ ከጥላሸቱ ጋር ይቀላቅለዋል ፤



ሥዕል 4 የጥቁር ቀለም ማዘጋጃ ጥሬ እቃዎች፡ የላምባ ጥላትና የዳጉሳ ሀሩር



ክትክታ-kətkəta/



ቀረጥ- Qärät̩

- የቅርቅሓን ሽልፋፎት አክስሎ ከጥላሸቱ ጋር መቀላቀል፤
- የቀንጠፋን ቅጠል አከስሎ ከጥላሸቱ ጋር መቀላቀል፤
- የበግ ቀንድ አቃጥሎ አሳርሮ ፈጭቶ ከጥላሸቱ ጋር መቀላቀል፤





ቀንጠፋ Qänṭäfa

- የኑግ ፍሬ አሳርሮ ቆልቶ በኋላም አንፈቅፍቆ አፍልቶ የላቦቱን ውሃ አጠራቅሞ እየጨመሩ ማሸት፤
- ማዋሐጃ የሚኾን ግራር ሙጫ ተጠራቅሞ ይጨመራል፤
- ይህ ሁሉ ተጠራቅሞ ንጹሕ ቦታ ይዞ የተጠቀሱትን መቃስማት ሁሉ አልሞና አለስልሶ በአንድ ላይ ቀላቅሎ አንፈቅፍቆ በጠንካራ ዕቃ አድርጎ በየጊዜው እያሹ ማቆየት፤ በመቆየቱና መታሸቱ ሲደረቅ ሐሩሩን እየጨመሩ ጠምዘዝ ባለ ጊዜ እንደገና ጠንክሮ ማሸት ነው።

## ለ. የሐሩር ዐይነት፡-

ሐሩር የሚባለው ለቀለሙ ወዝ የሚሰጥ የእህል ቅርጣን ነው፤ እርሱም ገብስም ስንዴም ፤ እንክርዳድም ቢሆን እንደተገኘ ይሆናል።

- *ከተገኘ ግን የዳጉሳ ሐሩር የበለጠ ይሆናል።*

እርሱንም ቆልቶ መቀቀል ነው፤ ከዚህም በኋላ የዚህ ውሃ በጣም ሳይቀጥን እየተዘፈዘፈ እየቆየ በየጊዜው ይጨመራል፤ በደንብ እንዲቦካም ሙቀት ቦታ ያስፈልጋል።

## ሐ. ቀለሙ ተፈላጊ ኸኖ የሚደርስበት ጊዜ

- ቀለሙ በዚህ ዐይነት ሲቦካ ቆይቶ በተፈላገው መንገድ እንዲሠራበት ሲፈለግ የሚፈጀው ጊዜ እንዳስተሻሸቱ ይሁን እንጅ ቢቸኩል **ሦስት ወር ድረስ** መቡካት አለበት፤ ያለዚያ ግን **ስድስት ወር ድረስ** ታሽቶ የወጣ እንደኾነ ጥፉ ቢሉት የማይጠፋ መሠረት ያለው ቀለም ይኾናል።
- ከዚያ በኋላ ልጥልጥ አድርጎ ለብዙ ዘመን ሊያገለግል እንዲችል በብዛት ከፍሎ ከፍሎ ማስቀመጥ።
- አንዳንድ ሰዎች ይህንን ብቻ ሥራየ ብለው እያወጡ የሚሸጡ ነበሩ።
- ነገር ግን አስተማሪዎችና ተማሪዎች ከመግዛት ይልቅ እራሳቸው ቢያወጡ ስለሚኾንላቸው በየጊዜው አራሳቸው ይሠራሉ።

# የቀይ ቀለም ሌሎች አዘገጃጀት

- ቀዩንና አረንጓዴውን ከአፈርና ከልዩ ልዩ ቅጠል በዚሁ መልክ ይቀምሙታል።
- ሌላውን ግን እነዚህን ሁለቱን በማገናኘት እየበጠበጡ ሚሰሩበት ልዩ ልዩ ኅብር ያላቸውን ቀለማት ይሰጣል።
- ሐረግ ይጥላሉ፤ ሥዕል ይስላሉ ።
- እንዲህ ኾኖ የወጣው ቀለም ብራናው ፈጽሞ ካላረጀና ካላለቀ አያረጅ አያፈጅ ወይም ብራናውን አይጎዳ አያበላሽ ተስማምቶ ይኖራል፤ አሁን የሚሠራበት የውጭ አገር ዘመናዊ ቀለም ግን ብዙ ዘይት ስላለበት ብራናውን ያበላሻል።




This Photo by Unknown Author is licensed under CC BY-NC

## መ. ተበጥብጦ የሚጻፍበት ጊዜ፦

- ልጥልጥ አንድም እንክብል የነበረው ቀልም ሊጻፍበት ሲያስፈልግ በቀለም ቀንድ ይበጠበጣል፤ እርሱም በደንብ እንዲቦካ 2 ቀን ያህል መዋል በግድ ያስፈልዋል።
- የቀለም ቀንድ የተባለውም ከክበት ቀንድ የሚሰራ የቀዩና የጥቁሩ ቀለም ተለይቶ ተሠርቶ ቅጹ አምሮ ለዚሁ ተግባር ብቻ ተዘጋጅቶ የሚገኝ እቃ ነው።

## ሠ. የሚጻፍበት ብዕር፡-

- የሚጻፍበትም ነገር ደግሞ በጥንት ጊዜ የዶሮ ወይም የአሞራ ላባ ነበር፤ አሁን ግን ሸንበቆ፣ የሴት ቀስት ይህንንም ከመሳሰሉት ዕጽዋት የሚገኝ ነው።
- ለዚህም ምሳሌ ጠቀስ ሲያደርጉ
- *"ወካህን የኀድር በመቃብር"* ይኸውም ካህን የሚተዳደረው በመቃ ብዕር ነው ማለታቸው።

# ፫ኛ. የብራና አወጣጥና የማውጫ መሣሪያዎች፦

ብራና ለማውጣት ብዙ ድካም ያለበት ብዙ ጊዜም የሚፈጅ ሥራ ነው።

ኹኖም መምህራኑ አንድም ጸሐፊዎቹ ሁሉ ሳይሰለቹ በየጊዜው ሲያወጡና በዚያም ሢሠሩ ይኖራሉ፤ አወጣጡም እንደሚከተለው ነው፦

1. ቆዳው ከውሃው ይነከራል፤እስኪበሰብስም ይቆያል
2. ቆዳው ከላይ በተጠቀሰው መልክ ርሶ ሲወጣ እንደ አልጋ በተሠራ እንጨት ይወጠራል፤
   a. ሥጋው ይፋቃል፤ ይታጠባል፤ ይራመማል፤
   b. ሲደርቅ ጸጉሩ ይፋቃል፤ በሻፎ ድንጋይ ይራመማል። በውስጥም በውጪም ይራመማል፤ ይታጠባል፤ ይጠራልም።
   c. ከጠራና ከነፃ በኋላ ሲደርቅ እንደ ቅጹ ዐይነት እየተቆረጠ እየተሠመረ ይጻፍበታል። ለዚህም የሚያስፈልጉ የተለያዩ መሣሪያዎች አሉ።



# Animal Types, Properties, Common Use, and Significance

| | | | |
|---|---|---|---|
| **Crocodile** | Thick, extremely durable, and features a distinctive scaly pattern that remains visible after processing. | Historically used for protective amulets and specialized scrolls intended for longevity. | Occasional use (modern reference); Offers unique qualities (Money Sen, 2011). |
| **Horse** | Produces large amounts of parchment due to hide size; typically, yellow-toned and stiff. | Historical use faced condemnation, as it was often associated with "magic" or secular texts in certain regions. | Considered unclean in Orthodox Ethiopian tradition (Winslow, S., 2011). |
| **Goat** | Durable, resistant to tearing, and possesses a variable texture that holds ink exceptionally well. | Primary material for religious books and general manuscripts for centuries. | Most common, widely available, associated with religious practices (Money Sen, 2011). |
| **Gazelle** | Extremely thin, fine-grained, and smooth; known for a velvety surface and high flexibility. | Historically prestigious; utilized for early Quranic codices and elite Islamic manuscripts (e.g., Kufic scripts) | Rare and expensive; valued for its historical association with luxury and spiritual devotion |




www.larkvi.com ©2011



# የብራና ማውጫ መሣሪያዎች፡-

- ማፈፊያ(ቢላ) የብረቱ ዐይነት ሞረድ የሚመስል የሥራው ዐይነት ስለቱ ዙሮ የገጠመ ሥጋውን የሚያስለቅቅበት መሣሪያ ነው።
- መላጫ (መጥረቢያ) የተባለ ነው። የቆዳው ጸጉር የሚላጨዕበት፣
- መወጠሪያ =አራት ማዕዘን ያለው እንጨት ብራናውን ቀዳውን የሚወጥርበት ነው።
- መሠቆሪያ(ለበቅ ፣ ዘንግ)= በቆዳው እየገባ ከግንዱ ጋር የሚያገናኝ ነው።
- መራመሚያ ድንጋይ= ዐይን ዐይን ያለው ሻፎ ድንጋይ ነው። እርሱም ጸጉሩን ከቆዳው ሥጋውንም የሚያስለቅቅ ለብራናውም ጥራትን የሚሸጥ ዕቃ ነው።
- ገመድ= መወጠሪያ



- ማስመሪያ፣ መሳፍቻ፣ ወሳፍቻ (ወስፌ)=መስመሩን የሚያሠምሩበት መሣሪያ ነው።
- መቁረጫት(መቀስ)=ብራናውን በቅጽ በቅጹ መቁረጫ፥
- መድመፅ= ለብራናው ለኸት የሚሰጥ ቀለም እንዲቀበል የሚያደርግ መሣሪያ ሲኾን 2 ዓይነት ነው።
    - የደቅ ሥራ ሸክላ= ሥጋውን የሚዳምጹበት
    - ነጭ ሸክላ=በጸጉር በኩል ያለውን ችግር የሚያቃልል መሣሪያ ነው።





- Hard-point ruling of each separate bifolium
- Today: use of modern measuring tools
- Use of template
- “Vertical pricks” done first
- “Text pricks” done in a way similar to “compass pricking.”
- Leaves pricked one by one, or several together?



Scheme 1



Scheme 2

# Glossary

1. **Folio: (folia, plu.):** a single leaf of a ms, both with the front (recto) and back (verso) sides available as writing spaces.
2. **Recto (ሥጋ፡ ገጽ) (r.)** : The front side of a folio. In an open manuscript, the recto side of the folio appears on the right-hand side.
3. **Verso (ጠጉረ፡ ገጽ) (v.)** : The second (reverse) side of a folio,

1. **Foliation:** It refers to the numbering of leaves in a manuscript.
2. **Bifolia:** a piece of sheet material folded to create two leaves of more or less equal size,
3. **Column**: lines of text arranged vertically on a folio. A folio can be set out in single column, double columns, three columns, or four columns.

# Glossary

- **Pricking:** Small holes made by the **scribe** at regular intervals along the edge of a leaf, used as a guideline for ruling.

  **Ruling:** Folios were ruled to provide guidelines for copying, and this ruling often consists of a frame with horizontal lines for writing. Ruling may be in ink, pencil, or dry point.
- **Quire:** Several **folios**, placed on top of each other, with a fold in the middle to form a codex.
- **Scribe:** The person who copied a text
- **Sewing holes:** the codex is sewn together during binding. Traces of previous bindings can therefore be seen in the holes that survive for stitching.
- **Rubricating:** The act of highlighting a particular part of a text by using red ink.

# Structure of the codex: the main elements




**Binding:**

- front board (1)
- back board (2)
- spine (3)
    - head (above)
    - tail (below)
- sewing (4)

(- leather cover)

(- endbands:)

(- headband (above))

(- tailband (below))

**Textblock** (5)

- quires
- bifolium/double leaves

bifolium consisting of two folia

## A. Production (Centers)



- ʾAndābet
- Dabra Libānos
- ʾAksum
- Tamben
- Gwəndā Gwənde

# እናመሰግናለን!!!

